6. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ አክሲዮኖቹን የሚጫረቱበትን ዋጋ ¼ በባንክ በተረጋገጠ ስፒኦ ወይም በባንክ በተመሠከረለት ቼክ ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚገዙበትን ዋጋ ከሚገልፁበት ሠነድ ጋር በታሸገ ኢንቬሎፕ ውስጥ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. ተጫራቾች አንድ ተጫራች ባቀረበው ዋጋ ላይ ተንተርሰው ዋጋ ማቅረብ አይችሉም፡፡
8. ተጫራቾች ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም ተቀባይነት ያለው ሌላ ማስረጃ ኮፒ እንዲሁም ድርጅቶች ከሆኑ አክሲዮኖቹ በሙሉ ኢትዮጵያዊ በሆኑ ዜጎች የተያዙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የመመሥረቻ ጽሑፍ ወይም ተቀባይነት ያለው ሰነድ ኮፒ ከጨረታው ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
9. ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይያያዝ የሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡
10. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ሳይያያዝ የሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡
11. የጨረታው አሸናፊዎች ያሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ የጨረታው አሸናፊ መሆናቸው ከተገለፀላቸው ቀን ጀምሮ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባንኩ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ገቢ ለማያደርጉ ተጫራቾች ጨረታው ተሰርዞ ያስያዙት ገንዘብ ለሚመለከተው አካል ገቢ ይሆናል፡፡
12. ማንኛውም በጨረታው አፈፃፀም ላይ ሊፈጠር የሚችል አለመግባባት ቢከሰት አግባብነት ባለው በሌሎች ሕጎችና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች የተደነገጉ ሕጎች ተፈፃሚነት አላቸው፡፡
13. ባንኩ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ**